# እውነትም እኛ ልዩ ነን

-በአበራ ለማ

ላለመስማማት ተዋደን
ላለመዋደድ ተስማምተን
ላለመኗኗር ተቧድነን
ላለመፋቀር ተቃቅፈን
ላለመጋባት ተጨጫጭተን
ይሄው ዙረን ዙረን... እዚያው ነን!
አጀብ ዘመናችንን ቸብችበን
በኪሳራችን ቶጅረን
የመጠላለፍ ጽዋችንን፤
ተራ በተራ.... ጨልጠን
ይሄው... ሃቻምናምና... ተነበርንበት
እዚያው ዞረን ዞረን... ግጥም አልንበት፤

እንግዲህ ማን አለ እንደኛ
ዞሮ ዞሮ ተነበረበት የተኛ
ማተብ ጠባቂ ሀቀኛ
ብርቅም አይደለን እኛ?...
እንደዋሊያ እንደኒያላ
እንደጭላዳ እንደምኒሊክ ድኩላ
በሌላው ዓለም የሌለን
እኛኑ ታግለን የጣልን
ቀይ ቀበሮን ተመስለን
ልዩነታችንን ያሳየን...

እውነትም እኛ ልዩ ነን
ማንም ማንም ያልበለጠን
ሃቻምናምና... ተነበርንበት
ፈጥነን ሮጠን በመገኘት
ወደር አቻ ያልተቸረን
እውነትም እኛ አንደኞች ነን።
እውነትም እኛ ልዩ ነን።

ይሄው ዙረን ዙረን... ተገጣጠምን
አንድ ሳንሆን ተማምለን
ለባለጊዜ ተመቻችተን
ጉሮሮ ለጉሮሮ ተያይዘን
እልካችንን ውጠን...
ማን አባቱ ሊደፍረን ብለን...
አንድ ራሳችንን አሸንፈን

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እንድ ራሳችንን ጥለን
እንድ ራሳችንን ገለን
ይሄው... ባሸናፊነት እንስቃለን
"እኛ ልዩ ነን..." እንላለን።
በራሳችን እንመጽታለን።
በኪሳራችን እንከብራለን።
በሽንፈታችን እንኮራለን።
አዎን... ልዩ ነን እንላለን።

አጀብ ጊዜያችንን ፈጅተን
ወገኖችንን ነውረን
እራሳችንን አጸጽሰን
ሌላ ሌላውን ኮንነን
ይሄው ዞረን ዞረን.... እዚያው ነን፤
የእዝን ንፍሮ እየቃምን
ስውር ሥርግ እየበላን
ለብቻችን እየሞትን
ለብቻችን እየሳቅን
ይሄው እኛነታችንን አልረሳንም
ሃቻምናምና... ተነበርነበት ዞር አላልንም
አንደኝነታችንን አለቀቅንም፤

ይሄው...
ላለመስማማት ተዋደን
ላለመዋደድ ተስማምተን
ላለመኗኗር ተቧድነን
ላለመፋቀር ተቃቅፈን
ላለመጋባት ተጫጭተን
ይሄው ዙረን ዙረን... እዚያው ነን
ሃቻምናምና... ተነበርንበት
ፈጥነን ሩጠን... ግጥም አልንበት፤
እውነትም እኛ ልዩ ነን
እውነትም እኛ ጀግኖች ነን
ወደር አቻ ያልተቸረን
አቻዮ ዲፌሮ የተሰኘን
ማንም ምንም ያልበገረን፤

እውነትም እኛ ልዩ ነን...
ወገን ወገኑን ሲበላ እያየን
የምንስቅ፥ የምንፈግግ ጉዶች ነን
ይሉኝታ ላይ ተኝተን
እንደር ብለን ተሸጠን
እየሞትን እኖራለን...
ሳንኖር እንሞታለን
እውነትም ልዩ ፍጡር ነን!
ዋልያ ነን የምንል
ጭላዳ ሆነን የምንል
ቀይ ቀብሮን የምንወክል

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እውነትም እኛ ልዩ ነን
ማንም ምንም ያልታከለን
አጀብኛ የታደለን...
እውነትም እኛ ልዩ ነን!!

(ኖርዌይ፥ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም.)

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com